# የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

## የምግብ ላኪ፣ አስመጪና አከፋፋይ

## ቁጥጥር መመሪያ

## 357/2013

ሀምሌ 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ......i
መግቢያ......1
ክፍል አንድ......2
ጠቅላላ......2
1. አጭር ርዕስ......2
2. ትርጓሜ......2
3. ዓላማ......3
4. የተፈፃሚነት ወሰን......3
ክፍል ሁለት......4
ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት......4
5. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ ማውጣት......4
6. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የማያሰጡ ሁኔታዎች......4
7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ነጥብ አሰጣጥ......4
8. የአድራሻ እና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ......5
9. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ምትክ ስለ መስጠት......5
10. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማሳደስ......5
11. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመመለስ......6
12. ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቀማመጥ......6
ክፍል ሦስት......6
ስለ ምግብ ማከማቻ ቦታ፣ አሰራርና ግብአቶች......6
13. የምግብ ንግድ ድርጅት ስለሚቋቋምበት አካባቢ......6
14. የምግብ ማከማቻ ህንፃ አሰራር......6
15. አስፈላጊ ግብዓቶችና ቁሳቁሶች......7
ክፍል አራት......9
የምግብ ንግድ ድርጅት ሰራተኞች የትምህርት ደረጃ፣ ጤንነትና ንፅህና......9
16. ስለ የምግብ ንግድ ድርጅት ቴክኒካል ኃላፊ......9
17. የምግብ ንግድ ድርጅት ቴክኒካል ኃላፊ የስራ ሃላፊነት......9
18. ከምግብ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰራተኞች ጤናና ደህንነት......9
ክፍል አምስት......10
ምግብ ወደ አገር ውስጥ ስለማስገባትና ወደ ውጭ አገር ስለመላክ......10
19. ምግብ ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት......10
20. በጤና ምስክር ወርቀት ላይ መካተት ስላለባቸው መረጃዎች......12
21. ስለ ምግብ የመጠቀሚያ ጊዜ......13
22. በምግብ ማሸጊያ ላይ መኖር ስላለበት መረጃ......13
23. በምግብ ፋብሪካዎች አማካኝነት ለላቦራቶሪ ምርመራ ስለሚመጡ ኬሚካሎች......14
24. ስለ ምግብ ማሸጊያ ቁጥጥር......15
25. የእርዳታ ድርጅት ስለሚያስመጣው ምግብ......15
26. ምግብን ወደ ውጭ ሀገር ስለ መላክ......15
ክፍል-ስድስት......16

ስለ ምግብ ማከፋፈል፣ ማከማቸትና ማጓጓዝ ..... 16
27. ምግብ ስለ ማከፋፈል ..... 16
28. ስለ ምግብ አከመቻቸትና አያያዝ ሁኔታ..... 16
29. ምግብ ስለ ማጓጓዝ ..... 17
30. የተበላሸ ወይም የጠቀሜታ ጊዜው ያለፈ ምግብ ስለ ማስወገድ..... 17
31. ምግብ ከገበያ ስለ መሰብሰብ ..... 17
ክፍል ሰባት ..... 18
አስተዳዳራዊ እርምጃዎች ..... 18
32. ስለ አስተዳዳራዊ እርምጃ እና ቅሬታ አቀራረብ ..... 18
33. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለ ማገድ ..... 18
34. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወርቀት ስለ መሰረዝ ..... 19
35. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ መመለስ ..... 19
ክፍል ስምንት ..... 20
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ..... 20
36. የምግብ መረጃ ስለመያዝ ..... 20
37. ምግብ ስለ ማስተዋወቅ ..... 20
38. መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለ ማድረግ..... 20
39. ስለ አገልግሎት ክፍያ ..... 21
40. የመተባበር ግዴታ..... 21
41. ስለ ተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች..... 21
42. መመመሪያው የሚፀናበት ጊዜ..... 21
እዝል 1 ..... 22
እዝል 2 ..... 23
እዝል 3 ..... 25
እዝል 4 ..... 26
እዝል 5 ..... 27
እዝል 6 ..... 28
እዝል 7 ..... 29
እዝል 8 ..... 30
እዝል 9 ..... 31
እዝል 10 ..... 32

## መግቢያ

በምግብ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩና የሚሰማሩ ድርጅቶች የሚልኩት፣ የሚያስመጡት ወይም የሚያከፋፍሉትን ምግብ ጥራትና ደህንነቱን በማረጋገጥ የህብረተሰቡን ጤና መጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምግቦች ጥራታቸውንና ደህንነታቸው የተረጋገጠ እና አግባብ ያለውን መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአሰራር ግልፅነትና ተጠያቂነት ማስፈን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡

ማንኛውም በምግብ ንግድ ስራ ላይ ለሚሰማራ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀፅ 55 (3) እና የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 299/2006 አንቀፅ 98 መሰረት ይህ የምግብ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ቁጥጥር መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የምግብ ላኪ፣ አስመጪና አከፋፋይ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 357/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በአዋጁና በደንቡ ላይ የተቀመጡት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

1) "ምግብ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀፅ 2 ንዑስ-አንቀፅ (1) ስር የተሰጠው ትርጓሜ እንደተጠበቀ ሆኖ በምግብ አምራች ድርጅት ተመርቶ ከአንድ በላይ በሆነ ክልል የሚዘዋወር ወይም ለውጭ አገር ገበያ ሽያጭ የተዘጋጀ ምርት ነው፤
2) "ምግብን ማጭረር" ማለት ምግብን ለጨረራ ሀይል በማጋለጥ ጎጂ ባክቴሪያዎችንና ሌሎች ተህዋስያንን በመግደል የቆይታ ጊዜውን ለማራዘም የሚከናወን ሂደት ነው፤
3) "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት በምግብ ንግድ ሥራ ላይየሚሰማራ ድርጅት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ነዉ፤
4) "የምግብ ንግድ ተቋም" ማለት በአዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀጽ 2 ንዑስ-አንቀጽ(2) መሠረት የምግብ ንግድን የሚያከናውንተቋም ሆኖ የምግብ ችርቻሮን አይጨምርም፤
5) "ምግብ ላኪ" ማለት ምግቦችን በየብስ፣ በባሕር ወይም በአየር ከኢትዮጵያ ዉጭ የሚልክ ሰው ነዉ፤
6) "ምግብ አስመጪ" ማለት ከሀገር ዉጭ የተመረቱ ምግቦችን በየብስ፣ በባሕር ወይም በአየር ወደ ሀገር ዉስጥ የሚያስገባ ሰው ነዉ፤
7) "ምግብ አከፋፋይ" ማለት ምግብን ከአንድ ክልል በላይ በማከፋፈል ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤
8) "የጤና ምስክር ወረቀት" ማለት እንደቅደም ተከተሉ ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ ወይም ወደ ውጪ ለሚላኩ ምግቦች አግባብ ካለው የውጪ አገር ወይም የሀገር ውስጥ አካል ወይም በባለሥልጣኑ ምግቡ ለሰው ምግብነት የሚውል መሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

9) "የምግብ ጥራት ምርመራ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት" ማለት ወደ አገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ወይም በአገር ውስጥ ለሚመረት ምግብ ይዘቱን የሚገልጽና ደህንነቱን የሚያረጋግጥ አግባብ ባለው የውጪ ሀገር ወይም የሀገር ውስጥ አካል ወይም በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

10) " ባለሙያ" ማለት የምግብ ንግድ ድርጅት በሚያስመጣው ወይም በሚልከው ወይም በሚያከፋፍለው ምግብ ደህንነትና ጥራት ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚሰራ ማንኛውንም ስራ በበላይነት የሚመራና የሚቆጣጠር ሰው ነው፤

11) "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤

12) "አዋጅ" ማለት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አሰተደደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 ነው፤

13) "አግባብ ያለው አካል" ማለት በአዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (40) መሠረት ባለስልጣኑ፣ የክልል መንግሥት አካል ወይም በህግ ሥልጣን የተሰጠው ሌላ አካል ነው፤

14) "ደንብ" ማለት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አሰተደደርና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 299/2006 ነው፤

15) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

16) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸ አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ በምግብ መላክ፣ ማስመጣትና ማከፋፈል ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛወም ሰው የሚልከውን፣ የሚያስመጣውን ወይም የሚያከፋፍለውን ምግብ ጥራትና ደህንነት በማረጋገጥ የህብረተሰቡን ጤና ማስጠበቅ ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

1) ይህ መመሪያ በሀገሪቱ በምግብ መላክ፣ ማስመጣትና ማከፋፈል ስራ ላይ በተሰማራ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2) ይህ መመሪያ የተጨማሪ ምግብና የጨቅላ ሕጻናት ምግብ መመሪያዎች ላይ የተደነገጉ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

### 5. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ ማውጣት

1) ማንኛውም ሰዉ ከባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያገኝ በምግብ መላክ፣ ማስመጣት ወይም ማከፋፈል ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡
2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያመለክት ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ ክፍል ሶስትና አራት ስር የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡
3) አመልካቹ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማሟላቱን በመግለጽ ተቋሙ እንዲታይለት ሲያመለክት ከሁለት ባላነሱ የባለሥልጣኑ ተቆጣጣሪዎች ድርጅቱ እንዲታይ ይደረጋል፡፡
4) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ላይ ከተዘረዘሩት መሰረታዊ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ወይም ከዛ በላይ ካለ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አይሰጥም፡፡

### 6. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የማያሰጡ ሁኔታዎች

1) የማከማቻ ክፍሉ ግድግዳና ወለል ቆሻሻ የማይዝና ሊታጠብ የሚችል ወይም በቀላሉ ሊጸዳ የሚችል ቀለም የተቀባ ካልሆነ፤
2) የማከማቻ ክፍሉ የተፈጥሮ ብርሃንና የአየር ዝውውር ከሌለው፤
3) ድርጅቱ የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቅ የሚያስፈልጋቸው ምግቦችን (እንደ ወተት፣ ስጋ፣ አሳና የመሳሰሉትን) የሚያከማች ከሆነና ምግቡን ለማከማቸትና ለማጓጓዝ የሚያስችል የማቀዝቀዥ መሳሪያና አማራጭ የሃይል ምንጭ ከሌለው፤
4) እንደ ምግቡ ባህሪይ ለማስቀመጥ የሚያስችሉ መደርደሪያዎች ወይም ፓሌቶች ካልተሟሉ፤ እና
5) በመስፈርቱ ላይ የተቀመጠዉ ባለሙያ ካልተሟላ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የማይሰጠው ይሆናል፡፡

### 7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ነጥብ አሰጣጥ

1) በዚህ ክፍል አንቀፅ 6 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በመመሪያው ክፍል ሦስትና አራት ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ቢያንስ 75% ማሟላት አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ነጥብ በቂ የሚሆነው ድርጅቱ በኢንስፔክሽን ወቅት የሚገኝ ማንኛውም ክፍተት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በማሟላት በአዝል 3 ላይ የተቀመጠውን የመተማመኛ ስምምነት ሰነድ ለመፈረም ግዴታ የገባና የተሰማማ ከሆነ ብቻ ይሆናል፡፡

## 8. የአድራሻ እና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ

ማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት ባለስልጣኑን ሳያስፈቅድ ድርጅቱን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካገኘበት አድራሻ ወደ ሌላ አድራሻ ማዘዋወር፤ የባለቤትነት ወይም ኃላፊ ለውጥ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## 9. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ምትክ ስለ መስጠት

ድርጅቱ የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ከሆነ ምትክ ሊያገኝ የሚችለው፡-

1) ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተበላሸበት ከሆነ የተበላሸዉን የምስክር ወረቀት ሲመልስ ፤
2) ድርጅቱ የብቃት ማረጋጋጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ከሆነ የጠፉበት ስለመሆኑ አግባብነት ካለው አካል ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ማረጋገጫ ሲያቀርብ፤ እና
3) አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም ይሆናል፡፡

## 10. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማሳደስ

1) ማንኛዉም የምግብ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ሊታደስለት የሚችለዉ የምስክር ወረቀቱ ካልታገደ፣ ካልተሰረዘ ወይም ድርጅቱ በራሱ ፈቃድ ስራዉን ካላቋረጠ ብቻ ይሆናል፡፡
2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የሚታደሰው፤
   ሀ) በባለስልጣኑ ለዚህ የስራ ዘርፍ የወጡ መመዘኛዎች የተጠበቁ ስለመሆናቸው በባለስልጣኑ ተቆጣጣሪዎች በሚደረግ ኢንስፔክሽን ሲረጋገጥ፤
   ለ) ተገቢው የአገልግሎት ክፍያ በደንብ ቁጥር 376/2008 መሰረት ሲከፍል ይሆናል፡፡

11. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመመለስ

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠው በኋላ በምርቱ ወይም አገልግሎቱ ላይ የዓይነት፣ የቦታ ለውጥ ሲያደርግና አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ጠይቆ ተቀባይነት ሲያገኝ፤
2) የባለቤትነት ለውጥ ሲኖርና ድርጅቱ ሲዘጋ ወይም
3) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የወሰደው ሰው በራሱ ፈቃድ ስራ ካቆመ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን መመለስ አለበት፡፡
4) በባለስልጣኑ በሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲመልስ ሲገደድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን መመለስ አለበት፡፡

12. ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቀማመጥ

ማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የዋናውን ቅጅ በግልፅ በሚታይ ቦታ ማስቀመጥ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለ ምግብ ማከማቻ ቦታ፣ አሰራርና ግብአቶች

13. የምግብ ንግድ ድርጅት ስለሚቋቋምበት አካባቢ

1) ማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት የድርጅቱን ስምና አድራሻ በግልጽ ሊነበብ በሚችል ቦታ ቢያንስ በአማርኛ ቋንቋ ፅፎ ድርጅቱ በሚገኝበት ቦታ ድርጅቱን ሊያመላክት የሚችል የውጭ ማስታወቂያ ሊያኖር ይገባል፡፡
2) ከነፍሳት መራብያ፣ ቆሻሻ መጣያ፣ ኬሚካልና መርዝ ከሚከማችባቸው ቦታዎች እንዲሁም በአጠቃላይ ምግብን ሊበክሉ ከሚችሉና በሰው ጤናና ደህንነት ላይ አደጋ ለሚያስከትሉ ነገሮች ተጋላጭ ያልሆነ፤ እና
3) አስፈላጊ የመሰረተ ልማት አውታሮች ማለትም እንደ መብራት፣ ውሀና መንገድ የተሟሉለት መሆን አለበት፡፡

14. የምግብ ማከማቻ ህንፃ አሰራር

1) ክፍሉ ከሚከማቸው ምግብ ባህሪይ አንፃር የምግብ መበከል የማያመጣና በምርቱ ጥራትና ደህንነት ላይ ተፅእኖ በማያሳድር መልኩ የተገነባ፤

2) ህንፃው ከድንጋይ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላ ወይም ከሌሎች ተመሳሳይ ቁሶች የተሰራ ሆኖ በክፍሉ ላይ ሙቀት የማያሳድር እና ቆሻሻ የማይዝና ሊታጠብ በሚችል ቀለም የተቀባ፤
3) የክፍሉ ስፋት እንደሚከማቸው የምግብ መጠንና ዓይነት በቂ ሆኖ ጥቅም ላይ የማይውል ምግብ ማቆያ ቦታ ያለው፤
4) በርና መስኮቱ ነፍሳት፣ ቆርጣሚ እንስሳትና ሌሎች ምግብን ሊበክሉ የሚችሉ ነገሮችን በማያስገባ መልኩ የተገነባ፤
5) ወለሉ በኮንክሪት፣ ሴራሚክ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ቁሶች የተሰራ ሆኖ በቀላሉ ሊፀዳ የሚችልና ውሀ የማያቁር፤
6) የክፍሉ ግድግዳ በሲሚንቶ፣ ኮንክሪት፣ ብሎኬት፣ ሴራሚክ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ቁሶች የተሰራ ሆኖ በቀላሉ የሚታጠብ፤
7) የክፍሎቹ ጣሪያ ሙቀት ሊቀንስ የሚችል ሆኖ ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃን የማያስገባ፤
8) ክፍሎቹ በቂ የተፈጥሮ ብርሀን የሚያስገቡና የአየር ዝውውር ያላቸው፤ እና
9) ድርጅቱ በቂ መፀዳጃ ቤት ያለው መሆን አለበት፡፡

## 15. አስፈላጊ ግብዓቶችና ቁሳቁሶች

1) በምግብ መደርደሪያ ላይ ሊቀመጡ የሚችሉና ክብደት የሌላቸው ምግቦች መደርደሪያ ከመሬት ቢያንስ 20 ሳ.ሜ ከፍ ብለው፣ ከግድግዳው ቢያንስ 50 ሳ.ሜ ርቀው፣ ከጣሪያዉ ቢያንስ 30 ሳ.ሜ ዝቅ ብለው እንዲሁም መደርደሪያዎቹ ቢያንስ 50 ሳ.ሜ ተራርቀው የተቀመጡ መሆን አለባቸው፡፡ ያለመደርደሪያ ለሚቀመጡ ምግቦች ከመሬት ቢያንስ 20 ሳ.ሜ ከፍ ብለው የተሰሩ ፓሌቶች መኖር አለባቸው፡፡

2) እንደ አካባቢውና እንደ ምግቡ ባሕሪ የክፍሎቹን የአየር ዝውውር ለመቆጣጠር የሚያስችል ቬንትሌተር ወይም የአየር ሁኔታ ማስተካከያ መኖር አለበት፡፡

3) በድርጅቱ ውስጥ ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው መሳሪያዎችና መደርደሪያዎች የማይዝጉ መሆን አለባቸው፡፡

4) ምግቡ ለእይታ የሚቀርብበት ወይም የሚቀመጥበት ማቴሪያል በቀላሉ ሊፀዳና ሊታጠብ የሚችል፣ የማይዝግ እንዲሁም ምግቡን ለቀጥተኛ የፀሀይ ብርሀን የማያጋልጥ መሆን አለበት፡፡

5) የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃው ክዳን ያለው መሆን አለበት፡፡

6) በድርጅቱ ውስጥ ለሚነሳ ድንገተኛ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳርያ ሊኖረው ይገባል፡፡

7) ድርጅቱ የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ መሳሪያ (First Aid Kit) ሊኖረው ይገባል፡፡

8) ድርጅቱ እንደየስራ ባህሪውና የምግቡ ዓይነት የሰራተኞች የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ ሊኖረው ይገባል፡፡

9) ድርጅቱ የቅዝቃዜ ሰንሰለታቸው መጠበቅ ያለባቸውን ምግቦች የሚያከማች ከሆነ የምግቡን ቅዝቃዜ ሰንሰለት ለመጠበቅ የሚያስችል ማቀዝቀዣ መሳሪያዎች የተገጠመለት ክፍል ወይም ራሱን የቻለ ማቀዝቀዣ እንዲሁም ምግቡን ለማጓጓዝ የሚያስችል ማቀዝቀዣ መሳሪያ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

10) ድርጅቱ የተለያዩ የማቀዝቀዣ መሳሪያዎች የሚጠቀም ከሆነ አማራጭ የሀይል ምንጭ ሊኖረው ይገባል፡፡

11) ድርጅቱ እንደ ስጋ፣ የተዘጋጁ ምግቦችና የመሳሰሉትን የሚያከማች ከሆነ በማከማቻ ክፍሎቹ መግቢያ በር አካባቢ የበራሪ ነፍሳት መያዣ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡

12) ድርጅቱ የሚያከማቸው ምግብ ስጋ ከሆነ የስጋ ማቀዝቀዣ ክፍሉ መስቀያዎቹ ከመሬት ቢያንስ 50 ሳ.ሜ ከፍ ብለው፣ ከጣሪያዉ ቢያንስ 50 ሳ.ሜ ዝቅ ብለው፣ ከግድግዳው ቢያንስ 40 ሳ.ሜ ርቀው የተቀመጡ መሆን አለባቸው፡፡

13) ድርጅቱ ትኩስ አትክልት፣ ፍራፍሬና የመሳሰሉትን ምግቦች የሚያከማች ከሆነ ምግቡን ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ ወይም ለማከማቸት የሚያስችል ከፕላስቲክ ወይም ከእንጨት የተሰሩ ሳጥኖች ሊኖሩት ይገባል፡፡

14) ድርጅቱ የውስጥ ጥራት ቁጥጥር ስርአት (Internal Quality Auditing System) ሊኖረው ይገባል፡፡

15) በድርጅቱ ውስጥ ለሚከናወኑ ተግባራት የአሰራር ስርአት (Standard Operating Procedure) ሊኖረው ይገባል፡፡

# ክፍል አራት
# የምግብ ንግድ ድርጅት ሰራተኞች የትምህርት ደረጃ፣ ጤንነትና ንፅህና

## 16. ስለ የምግብ ንግድ ድርጅት ቴክኒካል ኃላፊ

ማንኛውንም የምግብ አስመጪ፣ ላኪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት በቴክኒካል ሀላፊነት የሚመራ ሰው በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ቢያንስ 10ኛ ክፍል ወይም በቀድሞው የትምህርት ፖሊሲ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

## 17. የምግብ ንግድ ድርጅት ቴክኒካል ኃላፊ የስራ ሃላፊነት

1) ማንኛዉም ኃላፊ በድርጅቱ ከምግብ ደህንነትና ጥራት መጓደል ጋር ተያይዞ ለሚከሰቱ ማናቸውም የጤና ችግሮች ከድርጅቱ በተጨማሪ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2) ሀላፊ ድርጅቱ በሚያስመጣቸዉ፣ በሚያከፋፍላቸዉ ወይም በሚልካቸዉ ምግቦች ላይ የታዩ የጥራትና ደህንነት ለዉጥ ወይም ችግር መከሰቱን ሲያዉቅ ሁኔታዉን ወዲያውኑ ለድርጅቱ ዋና ሀላፊ ወይም ባለቤት ማሳወቅ እና አሰፈላጊውን እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

3) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ዋና ሀላፊ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ ቴክኒካል ባለሞያው ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 18. ከምግብ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰራተኞች ጤናና ደህንነት

1) ማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት ከምግቡ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊት በምግብ አማካኝነት ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አለበት፡፡

2) ድርጅቱ ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች በየስድስት ወሩ የጤና ምርመራ እንዲመረመሩ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

3) ማናቸውም ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች ማንኛውም በምግብ አማካኝነት የሚተላለፉ በሽታዎች እና ምልክቶች ካለባቸው ህክምናውን እስኪጨርሱ ድረስ ከስራ ገበታቸው መለየት ይኖርባቸዋል፡፡

4) ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች የግል ንጽህና አጠባበቅ የአሰራር ስርዓት መሰረት ቁጥጥርና ክትትል መደረጉን የሚያሳይ መረጃ መኖር አለበት፡፡

5) በድርጅቱ ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች እንደ ስራው ባህሪ በስራ ወቅት የምግብን ጥራትና ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

6) ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊትም ሆነ በስራ ላይ እያሉ የጤና አጠባበቅ ስልጠና በተለይም ስለመሠረታዊ የምግብ አያያዝና ደህንነት፣ ስለምግብ ባህሪያት፣ በምግብ ላይ የሚመጡ ተላላፊ በሽታዎችን የሚመለከቱና መሰል ስልጠናዎች መዉሰድ አለባቸው፡፡

## ክፍል አምስት
## ምግብ ወደ አገር ውስጥ ስለማስገባትና ወደ ውጭ አገር ስለመላክ

### 19. ምግብ ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት

1) ማንኛውም ሰው ምግብ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የሚችለው በሀገሪቱ ባሉ የመግቢያና መውጫ ኬላዎች ብቻ ሆኖ አስፈላጊው የጥራትና ደህንነት ፍተሻ የተደረገበት መሆን አለበት፡፡
2) ማናቸውም የኢትዮጵያ አስገዳጅ ደረጃ የወጣላቸው ምግቦች ወደ አገር ውስጥ በሚገቡበት ወቅት የሦስተኛ ወገን የጥራት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3) ምግቡ በመግቢያና መውጫ ኬላ በሚደርስበት ወቅት ስለ ምግቡ ጥራትና ደህንነት የሚገልፁ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፉ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፡፡
   ሀ. በድርጅቱ ባለቤት ወይም ህጋዊ ተወካይ የተፈረመ ማመልከቻ፤
   ለ. አዲስ ወይም የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ኮፒ፤
   ሐ. የአልኮል መጠጦችን ሳይጨምር ኦርጅናል የጤና ሰርተፍኬት (Original Health Certeficate) ፤
   መ. የስሪት አገር ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ኮፒ (Certeficate of Origin) ፤
   ሠ. የጉምሩክ ዲክላራስዮን ኮፒ (Custom Diclaration) ፤
   ረ. ቢል ኦፍ ሎዲንግ፤ኤርዌይ ቢል ወይም የመንገደኛ ወረቀት (Bill of Loading, Airway Bill or trakbill) ፤
   ሰ. ኢንቮይስ (Comercial Invoice) ፤
   ሸ. የእቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ ኮፒ (Packing List) ፤

ቀ. ምግቡ የተጨረረ ከሆነ የጨረራ ቅሪት መጠኑ የሰውን ጤና የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፤

በ. ተጨማሪ የምርት ሂደት ያልተካሄደበት የእንሰሳትና የእንሰሳት ተዋፅኦ ከሆነ የቬቴርነሪ ሰርተፊኬት፤

ተ. ተጨማሪ የምርት ሂደት ያልተካሄደበት አትክልትና ፍራፍሬ ከሆነ ኦርጅናል የፋይቶ ሳኒተሪ ሰርተፊኬት፤ እና

ቸ. ለሩዝ ኦርጅናል የፋይቶ ሳኒቴሪ ሰርተፊኬት ሊያሟላ ይገባል፡፡

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 (በ) እና (ተ) ላይ የተጠቀሱት ምግቦች በንዑስ አንቀፅ 3(ለ)እና (ሐ) የተጠቀሰው መስፈርት ተፈጻሚ አይሆንባቸውም፡፡

5) ለሳይንሳዊ ምርምር አገልግሎት የሚመጡ ምግቦች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 (ለ) የተጠቀሰው መስፈርት ተፈፃሚ አይሆንባቸውም፡፡

6) ለግል ፍጆታ፣ ለኤግዚብሽን ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት የሚውሉ ምግቦች ላይ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ 3 የተዘረዘሩ መስፈርቶች ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡ ሆኖም ሌሎች የጥራትና ደህንነት ቁጥጥር የሚካሄድባቸው ይሆናል፡፡

7) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለግል ፍጆታ ተብሎ የመጣው ምግብ ብዛት ያለው ከሆነና ለንግድ አላማ ይውላል ተብሎ ሲታሰብ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተዘረዘሩ መስፈርቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

8) በምግብ ፋብሪካዎች አማካኝነት ለምግብ ጥሬ እቃ ግብዓት ናሙናነት የሚመጡን በተመለከተ በአንቀፅ 3 (ሀ) እና (ለ) ከተጠቀሱት ውጭ ሌሎች የተዘረዘሩ መስፈርቶች ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡ ሆኖም ሌሎች የጥራትና ደህንነት ቁጥጥር የሚካሄድባቸው ይሆናል፡፡

9) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 8 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለናሙናነት የሚመጡ ምግቦችን በተመለከተ ምርቶቹ ለናሙናነት አገልግሎት ብቻ የሚውሉና በማንኛውም መንገድ ለህብረተሰቡ ሽያጭ አገልግሎት የማይውሉ ስለ መሆናቸው የሚገልፅ በድርጅቱ ሀላፊ የተፈረመ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

10) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 6 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኤግዚብሽን አገልግሎት የሚውሉ ምግቦች ሲያስመጣ ምርቶቹ ለዚሁ አገልግሎት የሚውሉ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ደብዳቤ አግባብ ካለው የመንግስት ተቋም ወይም ኤግዚብሽኑን ካዘጋጀው አካል ማምጣት ይጠበቅበታል፡፡

11) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3(ሐ) ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ሰርተፍኬት ከማይሰጡ ሀገራት የሚመጣ ምግብ ከሆነ ሀገሪቱ የጤና ሰርተፍኬት የማይሰጥባት ስለ መሆኗ መረጋገጥ አለበት፡፡

12) የመግቢያና መውጫ ኬላ ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተጠቀሱ መረጃዎች የተሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ አካላዊ ቁጥጥር ያካሂዳል፣ በምርቱ ጥራትና ደህንነት ላይ ጥርጣሬ ሲኖረውም እንደአግባቡ አስፈላጊውን ናሙና በመውሰድ የላቦራቶሪ ምርመራ እንዲደረግ ሊያዝ ይችላል፡፡

13) በዚህ አንቀፅ ንፅስ አንቀፅ (12) የተጠቀሰው የላብራቶሪ ምርመራ ውጤት በሀገሪቱ ደረጃ መሰረት ሲሆን ደረጃ ያልወጣለት ምግብ ከሆነ በኮዴክስ ኤልመንተሬስ ወይም ሀገሪቱ በተቀበለችው ደረጃ መሰረት የሚገለጽ ይሆናል፡፡

14) በምርቱ ላይ ተጨማሪ የላቦራቶሪ ምርመራ ማድረግ የሚያስፈልገው ከሆነ ምርቱ በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ሲቆይ ለብልሽት እንዳይዳረግ፤ ምርቱ አገር ውስጥ መወገድ የሚችል ከሆነ አስመጪው ድርጅት የላቦራቶሪ ውጤት ታውቆ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በመጋዘኑ ውስጥ ሳይሸጥና ሳይለውጥ እንደሚያስቀምጥ የውዴታ ግዴታ ሲገባ ምርቱ ከጉምሩክ እንዲወጣና በአስመጪው መጋዘን ታሽጐ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

15) ማንኛውም የምግብ ጭማሪ ለምግብ ዝግጅት እንደ ጥሬ ዕቃነት የሚያገለግል ስለ መሆኑ በኮዴክስ አሊመንተሪየስ የምግብ ጭማሪ ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ወይም በሀገራችን ደረጃ የተፈቀደ መሆን አለበት፡፡

16) ማንኛውም ልውጥ ሕያው ምግብ ወይም ከልውጥ ሕያዋን ዘር የተሰራ ምግብ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ በምግቡ ገላጭ ጽሁፍ ላይ ከልውጥ ሕያዋን ዘር የተሰራ ምግብ መሆኑ መጠቀስ አለበት፡፡

## 20. በጤና ምስክር ወርቀት ላይ መካተት ስላለባቸው መረጃዎች

ማንኛውም የጤና ምሰክር ወርቀት አግባብ ባለው አካል የተሰጠና ከ3 ወር በላይ ያልቆየ ኦርጅናል ሆኖ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች ያካተተ መሆን አለበት:-

1) የምግቡ አይነትና መጠን፤
2) የኢንቮይስ ቁጥር፤
3) የጤና ሰርተፊኬቱ የተሰጠበት ቀንና ዓመት፤
4) የጤና ምስክር ወርቀት ሰጪው አካል ስም፣ አድራሻና የኃላፊ ስምና ፊርማ፤ እንዲሁም
5) ለሰው ምግብነት ሊውል የሚችል መሆኑን፤ አግባብ ያለው የመንግስት አካል በአምራች ድርጅቱ ላይ በየጊዜው አስፈላጊውን የምግብ ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር እያደረገበት መሆኑን ወይም ለምግብ ዝግጅት በጥሬ ዕቃነት ስለ መዋሉ የሚግልጽ ፅሁፍ መያዝ ይኖርበታል፡፡

## 21. ስለ ምግብ የመጠቀሚያ ጊዜ

1) ማንኛውም ምግብ በባለስልጣኑ ተቆጣጣሪዎች ታይቶ የመግቢያ ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ የምግቡ የመጠቀሚያ ጊዜው 50 ፐርሰንት እና ከዚያ በላይ ሊሆን ይገባል፡፡
2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ አግባብነቱ በባለስልጣኑ የምግቦቹ አስፈላጊነት አገር ውስጥ ገብተው ጥቅም ላይ ከሚውሉበት ጊዜ አንፃር ታይቶ ሊወሰን ይችላል፡፡
3) የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከሶስት ወር በታች ለሆኑ ምግቦች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው በቀን፣ በወር እና በዓመት ተለይቶ በግልፅ መቀመጥ አለበት፡፡
4) የመጠቀሚያ ጊዜ የማይጠየቅባቸው የምግብ ዓይነቶች

   ሀ. ተጨማሪ የምርት ሂደት ያልተደረገባቸው አትክልት፣ ፍራፍሬና ጥራጥሬ፤

   ለ. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 (ሀ) እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ጥራጥሬ የመሳሰሉ ምግቦች ተጨማሪ የምርት ሂደት ተካሂዶባቸው የቅርፅና የመልክ ለውጥ ቢደረግባቸውም ሌላ ግብአት ካልተጨመረባቸው በስተቀር የመጠቀሚያ ጊዜ አይጠየቅባቸውም ሆኖም ግን የተመረተበት ቀን ሊጠቀስ ይገባል፤

   ሐ. ማንኛውም የአልኮል መጠኑ 10 ፐርሰንትና ከዚህ በላይ የሆነ መጠጥና

   መ. በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ምግቦች ናቸው፡፡

## 22. በምግብ ማሸጊያ ላይ መኖር ስላለበት መረጃ

1) ማንኛውም ምግብ በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ (Primary Packing) ላይ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተፃፈ ሆኖ ፅሁፉ በቀላሉ የማይለቅ ገላጭ ፅሁፍ ኖሮት ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

   ሀ. የምግቡን የንግድ ስም፤

   ለ.በምግቡ ውስጥ ያለው የንጥረ ነገር ዝርዝርና መጠን (ተጨማሪ የምርት ሂደት ለተከናወነባቸው)፤

   ሐ. ምግቡን ለማምረት ጥቅም ላይ የዋሉ ግብዓቶች ዝርዝር (ተጨማሪ የምርት ሂደት ለተከናወነባቸው)

   መ. የአምራች ወይም የአገር ውስጥ አስመጪ ወይም አለም አቀፍ አከፋፋይ ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፤

   ሠ. ምርቱ የተመረተበት አገር፤

   ረ. የምርቱ መጠቀሚያ ጊዜ፤

ሰ. ተጨማሪ የምርት ሂደት ለተከናወነባቸው ምግቦች የምርቱ መለያ ቁጥር (Batch Number) ፤

ሸ. እንደ ምግቡ ባህሪ የአጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ መያዝ አለበት፡፡

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 (መ) እንደተጠበቀ ሆኖ በምርቱ ላይ በአምራች ድርጅቱ ምትክ የአገር ውስጥ አስመጪው ወይም የአለም አቀፍ አከፋፋይ ድርጅቱ ስምና ሙሉ አድራሻ የተጠቀሰ ከሆነ ምርቱን ባመረተው ድርጅትና በአገር ውስጥ አስመጪው ወይም በአለም አቀፍ አከፋፋይ ድርጅቱ መካከል የተደረገ ህጋዊ ስምምነት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

3) ማንኛዉም ገላጭ ፅሑፍ በግልፅ የሚነበብና በቀላሉ ከምርቱ ላይ የማይነሳ መሆን አለበት፡፡

4) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1 እና 3) እንደተጠበቁ ሆኖ የምግብ ጭማሪ ማሸጊያ ገላጭ ጽሑፍ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ. በማሸጊያው ላይ በግልፅ "የምግብ ጭማሪ" የሚል ገላጭ ፅሁፍ እና

ለ. የምግቡን የአጠቃቀም፣ የአያያዝ ሁኔታ እና መደረግ ስላለበት ጥንቃቄ መግለጽ አለበት፡፡

5) ማንኛውም የምግብ ገላጭ ጽሑፍ አቀራረብ በማንኛውም መልኩ ምግቡ የሰውን በሽታ እንደሚያድን፣ ለማከም አገልግሎት እንደሚውል ወይም ሌላ ምግብ የሚተካ እንደሆነ የሚገልጽ መሆን የለበትም፡፡

6) በተጨረረ ምግብ ማሸጊያ ገላጭ ፅሁፍ ላይ ምግቡ የተጨረረ ምግብ እንደሆነና የጨረራ ቅሪት መጠኑን የሚገልፅ መረጃ መኖር አለበት፡፡

7) ልውጥ ህያው ምግብ ወይም ከልውጥ ሕያው ዘር ወይም አካል የተዘጋጀ ምግብ ማሸጊያ ገላጭ ፅሁፍ ላይ ምግቡ ልውጥ ህያው ምግብ እንደሆነ የሚገልፅ መረጃ መኖር አለበት፡፡

## 23. በምግብ ፋብሪካዎች አማካኝነት ለላቦራቶሪ ምርመራ ስለሚመጡ ኬሚካሎች

1) ማንኛውም የምግብ ፋብሪካ ለላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችን በሚያመጣበት ወቅት ቁጥጥሩ በፋርማሲስቶች የሚካሄድ ይሆናል፡፡

2) ማንኛውም የምግብ ፋብሪካ ለላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችን በሚያመጣበት ወቅት አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 3 (ሀ፣ ለ፣ መ፣ ሠ፣ ረ፣ ሰ እና ሸ) የተጠቀሱ መረጃዎች ሲሚሉና በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ (Primary Packing) ላይ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተፃፈ ገላጭ ፅሁፍ ኖሮት ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ. የኬሚካሉን የንግድ ስም፤

ለ. የአምራች ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፤

ሐ. ምርቱ የተመረተበት አገር፤

መ. የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ እንደ አግባብነቱ፤

3) ለሚመጡ ኬሚካሎች የጥራት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (certificate of analysis) ወይም የኬሚካሉን የደህንነት ማረጋገጫ (material safety data sheet) መቅረብ አለበት፡፡

## 24. ስለ ምግብ ማሸጊያ ቁጥጥር

ማንኛውም አስመጪ ድርጅት የምግብ ማሸጊያዎችን በሚያመጣበት ወቅት በአንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 3 (ሀ፣ ለ፣ መ፣ ሠ፣ ረ፣ሰ እና ሸ) እንዲሁም በአንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 1(መ እና ሠ) ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 25. የእርዳታ ድርጅት ስለሚያስመጣው ምግብ

ማንኛውም የእርዳታ ድርጅት ምግብ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የሚችለው በአንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 3 (መ) ከተጠቀሰው መስፈርት ውጭ የተዘረዘሩ መስፈርቶች ሲያሟላና እርዳታ ከሚቀበለው አካል የተሰጠ የትብብር ደብዳቤ ሲኖረው እና ስለ እርዳታ ሰጪነቱ የተሰጠውን ምስክር ወረቀት ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

## 26. ምግብን ወደ ውጭ ሀገር ስለ መላክ

1) ማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት ወደ ውጭ ሀገር ምግብ ለመላክ የጤና ማረጋገጫ ምሰክር ወርቀት ሲፈልግና ተገቢውን መረጃዎች ሲያቀርብ ከባለስልጣኑ ማናቸውም የመግቢያና መውጫ ኬላዎች ከሚገኙ ቢሮዎች ማግኘት ይችላል፡፡
2) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ(1) መሰረት የጤና ምሰክር ወረቀት ለመስጠት የምግቡ ላኪ ድርጅት ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዳለው እና ምግቡ ደረጃውን በጠበቀ አስተሻሸግ የታሸገና በማሸጊያው ላይ የተሟላ ገላጭ ፅሁፍ መኖሩን ሲያረጋግጥ ይሆናል፡፡
3) የምግብ ላኪ ድርጅቱ ለአትክልት፣ ፍራፍሬ ወይም ጥራጥሬ ወይም ስጋ የጤና ሰርተፊኬት ለማግኘት ከፈለገ እንደ ቅደም ተከተሉ የፋይቶ ሳኒተሪ ወይም ቬቴሪነሪ ሰርተፊኬት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

4) አንድ የጤና ሰርተፊኬት የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ ጭነት (Consignment) ብቻ ነው፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2) ላይ የተጠቀሰው በጥቃቅንና አነስተኛ ምግብ አምራች ተቋማት ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ነገር ግን ፍቃድ ከሰጣቸው አካላት የትብብር ደብዳቤ ማምጣት አለባቸው፡፡

## ክፍል-ስድስት
## ስለ ምግብ ማከፋፈል፣ ማከማቸትና ማጓጓዝ

### 27. ምግብ ስለ ማከፋፈል

1) ማንኛውም የምግብ አከፋፋይ ድርጅት ምግብ መግዛት የሚችለው በባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠው የምግብ አስመጭ ድርጅት ወይም ከአገር ውስጥ ምግብ አምራች ድርጅት ብቻ ይሆናል፡፡

2) ማንኛውም የምግብ አካፋፋይ በማጓጓዝም ሆነ በማከማቸት ሂደት ወይም በማንኛውም ምክንያት ብልሽት ያልደረሰበትና ተገቢውን የደህንነትና ጥራት ደረጃ የጠበቀ ምግብ ብቻ ማከፋፈል አለበት፡፡

### 28. ስለ ምግብ አከመቻቸትና አያያዝ ሁኔታ

1) ድርጅቱ ምግቡን ምግብ ሊበክሉ ከሚችሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችና ሌሎች በካይ ነገሮች ጋር አብሮ ማከማቸት የለበትም፡፡

2) የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜአቸዉ ያለፈባቸው ምግቦች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው እንዲሁም ከሌሎች ምግቦች ተለይተው ጥቅም ላይ እንደማይውሉ የሚገልፅ ፅሁፍ በመለጠፍ ለዚሁ አላማ በተዘጋጀ ቦታ መቀመጥ አለባቸው፡፡

3) በተለየ የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቅ የሚያስፈልጋቸው ምግቦች የቅዝቃዜ ሰንሰለት በጠበቀ ሁኔታ መከማቸት አለባቸው፡፡

4) ማንኛውም ምግብ የሚከማችበት መጋዘን ንፁህ፣ ደረቅ፣ ቀዝቃዛ፣በቂ የተፈጥሮ ብርሃን የሚያስገባ እና ከቆርጣሚ እንስሳትና ተባይ ነፃ መሆን አለበት፡፡

5) በእያንዳንዱ የምርት ዓይነትና መጋዘን ላይ የምርቱን ዓይነት፣ ምርቱ ያለበትን ሁኔታ (አያያዝ፣ አቀማመጥና የቆይታ ጊዜው ያለበትን ደረጃ) እና ሌሎች ስለ ምግቡ የሚገልፁ መረጃዎች በየጊዜው መለጠፍ አለባቸው፡፡

## 29. ምግብ ስለ ማጓጓዝ

1) ማንኛውንም ሰው ምግብን ለብክለት በሚያጋልጥ ሁኔታ ማጓጓዝ የለበትም፡፡
2) ምግብን ለማጓጓዝ የሚያገለግል ማጓጓዣ እቃ ንፁህ፣ ደረቅና ምግብን ሊበክሉ ከሚችሉ ከፀሐይ፣ ከአቧራና ከማናቸውም እርጥበት አዘል ወይም ሌሎች ነገሮች ምግቡን የሚከላከል መሆን አለበት፡፡
3) ከምግብ ጋር የሚቃረን ባህሪ ያለው ወይም ምግብን ሊበክል የሚችል ማንኛውም ዓይነት እቃ በተጫነበት ወይም በተቀመጠበት የመጓጓዣ እቃ ምግብን መጫን ወይም ማጓጓዝ የተከለከለ ነው፡፡
4) የቅዝቃዜ ሰንሰለታቸው መጠበቅ ያለባቸው ምግቦች ተገቢውን የቅዝቃዜ መጠን ሊጠብቅ በሚችል ማቀዝቀዣ በተገጠመለት እቃ መጓጓዝ አለባቸው፡፡

## 30. የተበላሸ ወይም የጠቀሜታ ጊዜው ያለፈ ምግብ ስለ ማስወገድ

1) ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ ምግብና ምግብ ነክ ሸቀጥ ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ወይም በሀገር ውስጥ እንዲወገድ መደረግ አለበት፤
2) ከምግቡ ባህሪ አኳያ አገር ውስጥ ሊወገድ የማይችል ከሆነና ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ሲወሰን የባለስልጣኑ ተቆጣጣሪ ኬላው ለሚገኝበት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደብዳቤ መፃፍ አለበት፤
3) በሀገር ውስጥ እንዲወገድ የሚደረግ ከሆነ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ተቆጣጣሪዎች በተገኙበት በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አዋጅና ደንብ መሠረት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች በተውጣጣ ኮሚቴ አማካይነት አካባቢያዊ ተፅዕኖ በማያሳድር መልኩ እንዲወገድ መደረግ አለበት፤
4) ወደመጣበት ሀገር የመመለስም ሆነ በሀገር ውስጥ ለማስወገድ ሂደት የሚያስፈልገውን ወጪ በባለንብረቱ ይሸፈናል፤

## 31. ምግብ ከገበያ ስለ መሰብሰብ

የምግብ ንግድ ድርጅቱ ምርቱ ላይና ከምርቱ ጋር ተያይዞ ችግሮች ሲከሰቱ ምርቶቹን ከገበያ የመሰብሰብ ሃላፊነት አለበት፡፡

## ክፍል ሰባት
## አስተዳዳራዊ እርምጃዎች

### 32. ስለ አስተዳዳራዊ እርምጃ እና ቅሬታ አቀራረብ

1) የዚህን መመሪያ ወይም ሌላ አግባብ ያለውን የምግብ ደህንነት እና ጥራት ቁጥጥር ህግ የጣሰ ማንኛውም ሰው ባለስልጣኑ ባወጣው የአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ እና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ መሰረት እንደ አግባቡ በነጠላ ወይም በአንድነት አንድ ወይም ከዚያ በላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡
2) በዚህ ክፍል መሰረት የሚወሰዱ አስተዳዳራዊ እርምጃዎች በባለስልጣኑ የአስተዳዳራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ መሰረት ሆኖ በአስተዳደራዊ እርምጃው ላይ ቅሬታ ካለ አቤቱታውን በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ባለስልጣኑ ላቋቋመዉ ቅሬታ ሰሚ አካል መቅረብ ይኖርበታል፡፡
3) ቅሬታ የቀረበለት ቅሬታ ሰሚ አካል ቅሬታውን አጣርቶ በ30 ቀናት ውሰጥ ምላሽ መሰጠት ይኖርበታል፡፡

### 33. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለ ማገድ

ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የህግ ጥሰት ከተፈጸመ እንደ ህግ መተላለፉ መጠንና ባህሪ የምግብ ንግድ ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከአንድ ወር እስከ ስድስት ወር ለሚደርስ ጊዜ ይታገዳል፡-

1) ባለስልጣኑን ሳያስፈቅድ ተቋሙ የቦታ አድራሻ ላይ ለዉጥ ካደረገ፤
2) የቅዝቃዜ ሰንሰለት ሊጠበቅላቸው የሚገቡ ምግቦችን የቅዝቃዜ ሰንሰለታቸው በማይጠብቅ ሁኔታ ካጓጓዘ፣ ካከማቸ ወይም ሲሸጥ ከተገኘ፤
3) ባለሥልጣኑ በድርጅቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ለሚያደርጋቸው ማንኛውም የኢንስፔክሽን ስራዎች እንቅፋት የፈጠረ እንደሆነ፤
4) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካወጣበት ምርት ውጪ ካስመጣ ወይም ካከፋፈለ፤
5) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን በህገ ወጥ መንገድ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ካስተላለፈ፤
6) ድርጅቱ የጽህፍ ማስጠንቀቅያ ተሰጥቶት የማያስተካክል ከሆነ፤
7) አግባብ ባለዉ የመንግስት አካል  የንግድ ፈቃዱ ከታገደ (ለተመሳሳይ ጊዜ)፤ ወይም
8) ሌሎች ተመሳሳይ ጥፋቶች ሲፈፅም ከተገኘ፡፡

## 34. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወርቀት ስለ መሰረዝ

ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የህግ ጥሰት ከተፈጸመ እንደ ህግ መተላለፉ መጠንና ክብደት የምግብ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እስከ ሁለት አመት ለሚደርስ ጊዜ ይሰረዛል፡-

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተገኘው በሐሰተኛ ሰነድ ወይም በተጭበረበረ መንገድ መሆኑ ከተረጋገጠ፤
2) ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶችን ሳይጨምር ሕጋዊና ወቅታዊ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ፈቃድ ከሌለው ድርጅት ምግብ ከገዛ ወይም በማንኛውም መንገድ ከተቀበለ ወይም ፈቃድ ለሌለው አከፋፋይ ድርጅት ከሸጠ፤
3) የተበላሸ፣ የአገልግሎት ዘመን ያለፈበት፣ ገበያ ላይ እንዳይውል የታገደ፣ ስለምርቱ ሁኔታ ገላጭ ጽሑፍ የሌለው ወይም አሳሳች ገላጭ ጽሑፍ ያለው ምግብ የያዘ፣ የሸጠ ወይም ያከፋፈለ ወይም የከለሰ፣ አስመስሎ ያቀረበ፣ በሕገ ወጥ መንገድ ምግብ የያዘ ወይም ይህንን ስራ መከናወኑን አውቆ ምግቡን ከያዘ፣ ከሸጠ ወይም ካከፋፈለ
4) ድርጅቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ (11) መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን በወቅቱ ካላሳደሰ፤
5) ድርጅቱ አግባብ ባለው ሌላ አካል በንግድ ስራው እንዳይቀጥል ፈቃዱ ከተሰረዘ፤
6) ድርጅቱ በባለስልጣኑ የተጣለበትን እገዳ በመተላለፍ ስራውን ከቀጠለ፤
7) ድርጅቱ ስለእገዳ የተቀመጡትን ተመሳሳይ ጥፋቶች በሶስት አመት ጊዜ ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ ፈጽሞ ሲገኝ፤
8) ሌሎች ተመሳሳይ ጥፋቶች ሲፈጽም ከተገኘ፡፡

## 35. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ መመለስ

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘ፣ ከታገደ፣ በተቀመጠው የእድሳት ጊዜ ገደብ ሳይታደስ ከቀረ በሦስት የስራ ቀናት ውስጥ መመለስ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሰረት ስለተመለሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለሚመለከተው አካል ባለሰልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 36. የምግብ መረጃ ስለመያዝ

1) ማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት ስለአስመጣው፣ ስለአከፋፈለው፣ ስለላከው፣ ስለተበላሸ፣ የመጠቀሚያ ጊዜ ስላለፈበት፣ ስለተወገደ ምግብና ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ሰነዶች በአግባቡ የመያዝና በባለስልጣኑ ሲጠየቅም የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

2) ድርጅቱ ምግቡን የገዛበትና የሸጠለት ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ ጨምሮ ዝርዝር ኢንቮይሶች፣ ደረሰኞች፣ የክምችት መቆጣጠሪያ ስቶክና ቢን ካርዶች እና ሌሎች መረጃዎች የምግብ መጠቀሚያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ቢያንስ ለአንድ አመት ያህል መያዝ አለበት፡፡

3) ማንኛዉም የምግብ ንግድ ድርጅት በቴክኒካል ባለሞያነት የሚያሰራዉን ባለሙያ የትምህርት ማስረጃዎች እና ዉል ስምምነት ሊኖረዉ ይገባል፡፡

4) የመጋዘኑ ይዞታ በድርጅቱ ባለቤት ይዞታ ስር ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ሊኖረው ይገባል፡፡ ሆኖም መጋዘኑ በኪራይ ከሆነ በውል እና ማስረጃ የተረጋገጠ የኪራይ ውል ማስረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

### 37. ምግብ ስለ ማስተዋወቅ

ማንኛዉም የምግብ ንግድ ድርጅት በማንኛውም የማስታወቂያ መንገድ ተጠቅሞ ምግብ ማስተዋወቅ የሚችለው ባለስልጣኑ ባወጣው የምግብ ማስታወቂያ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

### 38. መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለ ማድረግ

1) ባለሥልጣኑ የወሰደውን ማንኛውም አስተዳዳራዊ እርምጃ በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የቅሬታ አቀራረብ ጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ ወይም ቅሬታ ሰሚ አካሉ ጉዳዩን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ መረጃዎቹን ለህብረተሰቡ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2) ባለሥልጣኑ በማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት ያገኛቸው የአሰራር ግድፈቶች፣ የተረጋገጡ ተጨባጭ ጥቆማዎች ሲያገኝና መረጃው ለሕብረተሰቡ ባለመነገሩ በህብረተሰቡ ጤና ላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላልተብሎ ሲታመን መረጃው በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

39. ስለ አግልግሎት ክፍያ

ማንኛዉም የምግብ ንግድ ድርጅት በባለስልጣኑ ለሚሰጠው አገልግሎት በደንብ ቁጥር 370/2008 በተደነገገው መሠረት የአገልግሎት የክፍያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

40. የመተባበር ግዴታ

ባለስልጣኑ ይህን መመሪያ ለማስፈፀም እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማናቸውም የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

41. ስለ ተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

1) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ ሰርኩላር ደብዳቤ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡
2) የምግብ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 3/2004 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

42. መመመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመስከረም/2009 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር**

**አዝል 1**

የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

**Ethiopian Food, Medicine & Healthcare Adminstration and Control Authority**

**በድርጅቱ ላይ መኖር ያለበት ዝቅተኛ የሽንት ቤት ብዛት በሰራተኛ መጠን**

| ተ.ቁ. | የሰራተኞች ብዛት ለእያንዳንዱ ጾታ | ዝቅተኛ የሽንት ቤት መጠን |
|---|---|---|
| 1. | 1 to 15 | 1 |
| 2. | 16 to 35 | 2 |
| 3. | 36 to 55 | 3 |
| 4. | 56 to 80 | 4 |
| 5. | 81 to 110 | 5 |
| 6. | 111 to 150 | 6 |
| 7. | Over 150 | 1 ተጨማሪ ሽንት ቤት ለእያንዳንዱ 40 ተጨማሪ ተቀጣሪ ሰራተኛ |

የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

**Ethiopian Food, Medicine & Healthcare Adminstration and Control Authority**

## የምግብ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት በተቆጣጣሪዎች የሚሞላ የኢንስፔክሽን ቅፅ

የድርጅቱ ስም ____________________
የምርት ዓይነት ____________________
ድርጅቱ የሚገኝበት አድራሻ፡ ክልል-----------------------
ክፍለከተማ _______________________________ወረዳ _______________ከተማ________ቀበሌ
የቦታው ልዩ መጠሪያ _____________________
በድርጅቱ አካባቢ የሚገኝ ማንኛውም የተለመደ ቋሚ ተቋም -------------------------
ስልክ ቁጥር __
የድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ _________________________________

| | ዝርዝር መለኪያዎች | ዝርዝር መለኪያዎች | የታዩ ክፍተቶች | የመመዘኛ ነጥብ | የተሰጠው ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|
| **1** | የአካባቢ ሁኔታ | | | **10** | |
| ሀ | ድርጅቱ የተቋቋመበት ቦታ ለምግብ ብክለት ያለው ተጋላጭነት | ምግብን ሊበክሉ ከሚችሉና የሰውን ጤና ሊጎዱ ለሚችሉ ነገሮች ተጋላጭ ያልሆነ | | 4 | |
| ለ | የማካመቻዉ ክፍሉ ከሰዉ መኖሪያ ቦታ የመለየት ሁኔታዉ | | | 3 | |
| ሐ | የመሰረተ ልማት ሁኔታ | መብራት፣ ውሃ፣መንገድ የተሟሉበት መሆኑ | | 3 | |
| **2** | የህንፃው አሰራር ሁኔታ | | | **46** | |
| ሀ | የህንጻው አቀማመጥና የከፍታ ሁኔታ | ከሚከማቸው ምግብ ባህሪ አንጻር የምግብ መበከል የማያመጣና በምርቱ ጥራትና ደህንነትላይ ተጽኖ የማያሳድር መሆኑ | | 4 | |
| ለ | ህንፃው የተገነባበት ቁሰ ሁኔታ | ወይም ሌላ ተመሳሳይ ቁሶች የተሰራ ሆኖ በክፍሉ ሙቀት ላይ ተጽኖ የማያሳድር፣በቀላሉ ሊጸዳ | | 8 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚችል መሆኑ | | | |
| ሐ | ድርጅቱ ከሚያከማቸው የምግብ መጠን አንፃር የክፍሎቹ ስፋት ሁኔታ | ድርጅቱ እንደሚከማቸው የምግብ መጠንና አይነት በቂ የሆነ | | 8 | |
| መ | የተለየ የምግብ ማከማቻ ክፍል፣የተበላሹ ምግቦች ማቆያ ቦታ ሁኔታ | ጥቅምላይ የማይውል ምግብ ማቆያ ክፍል ያለ | | 10 | |
| ሠ | የማከማቻ ክፍሉ ጣሪያ የተሰራበት ማተሪያል ሙቀትና ከቀጥተኛ የፀሀይ ብርሃን የመከላከል አቅሙ | የክፍሉ ጣሪያ ሙቀት ሊቀንስ የሚችል ሆኖ ቀጥተኛ የጸሃይ ብርሃን የማያስገባ | | 5 | |
| ረ | የህንፃው በርና መስኮት ምግብን ሊበክሉ ከሚችሉ ነገሮች የመከላከል አቅሙ | ነፍሳት፣ቆርጣሚ እንስሳትና ምግብን ሊበክሉ የሚችሉ ነገሮችንና ቀጥተኛ የጸሃይ ብርሃን የማያስገባ | | 6 | |
| ሰ | የቆሻሻ አያያዝ ሁኔታ | የደረቅና የፍሳሽቆሻሻ ማስወገጃ መኖሩ | | 5 | |
| **3** | **አስፈላጊ ግብአቶችና ቁሳቁሶች** | | | **27** | |
| ሀ | የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ መሳሪያ መኖሩን | የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ መሳሪያ መኖሩ | | 5 | |
| ለ | የድንገተኛ እሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ መኖሩን | የድንገተኛ እሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ መኖሩ | | 6 | |
| ሐ | የምግብ ስርጭት መረጃ መያዣ ስርዓት መኖሩን | | | 6 | |
| መ | እንደ ምግቡ አይነት የሰራተኞች የደህንነት መጠበቂያ አለባሳት መኖራቸው | እንደ ምግቡ አይነት የሰራተኞች የደህንነት መጠበቂያ አለባሳት መኖራቸው | | 10 | |
| 4 | **የሰው ሀይል** | | | **17** | |
| ሀ | | በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ 10ኛክፍል ወይም በቀድሞው 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ቴክኒካል ባለሙያ መኖሩ | | 8 | |
| ለ | የጤና ምርመራ ሁኔታ | ከምግቡ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሰተኞች በምግብ አማካኝነት ከሚተላለፉ በሽታዎች ነጻ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ መኖሩ | | 7 | |

**አዝል 3**

የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

**Ethiopian Food, Medicine & Healthcare Adminstration and Control Authority**

## በኢንስፔክሽን ወቅት የተገኙ ክፍተቶች ለማሟላት ከድርጅቱ ጋር የሚገባ መተማመኛ ሰነድ

1. የድርጅቱ ስም ____________________ የምርት ዓይነት ________________
2. ድርጅቱ የሚገኝበት አድራሻ ________________ ክልል __________________ ዞን/ክፍለ ከተማ ወረዳ______ ከተማ _____ ቀበሌ ____ የቤት ቁጥር _____ ልዩ መጠሪያ ____________ ስልክ ቁጥር _________
3. የድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ ______________________

| ተ ቁ | በድርጅቱ ውስጥ የተገኙ ክፍተቶች | በድርጅቱ መወሰድ ያለባቸው የማሰተካካያ እርምጃዎች | የጊዜ ወሰን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

| | |
|---|---|
| የኢንስፔክተሩ ስም ፊርማ<br>1. ____________________ ________<br>2. ____________________<br>3. ____________________ ________<br>ቀን ____________________ | የድርጅቱባለቤት/ተወካይ ስም ____________<br>ፊርማ ________<br>ቀን____________________ ________ |

ማሳሰቢያ

1 ድርጅቱ የተቀመጠውን መስፈርት ከ50 ፐርሰንት በላይ አማልቶ ፍቃድ የሚሰጠው ከሆነ ጉድለቶችን ለማስተካከል ይህ የመተማመኛ ቅፅ በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ1ኮፒ ለድርጅቱ የሚሰጥ 2ኛ ኮፒ ከድርጅቱ ፋይል ጋር ይያዛል፣ 3ኛ ኮፒ ሊአንስፔክሽንና ሰረቬላንስ ዳይሬክቶሬት ለክትትል ይሰጣል፡፡

2 ድርጅቱ መስፈርቱን ሳያሟላ ቀርቶ በድጋሚ ፈቃድ ለማውጣት የሚመለሰ ከሆነ ይህ የመተማመኛ ቅፅ በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ1ኛ ኮፒ ለድርጅቱ የሚሰጥ 2ኛ ኮፒ ከድርጅቱ ፋይል ጋር ይያያዛል፡፡

3 ድርጅቱ በገባው የመተማመኛ ሰነድ መሰረት ክፍተቶቹን በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ካላሟላ አግባብ ባለው ህግ መሰረት አስተዳዳራዊ እርምጃ

የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን
Ethiopian Food, Medicine & Healthcare Adminstration and Control Authority

## የምግብ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

## Certificate of Competence for Food Export/Import/Wholesale Organization

ቁጥር ___________________
ቀን ____________________
የድርጅቱ ስም ______________________ የንግድ ስራ ዓይነት_____________________________
Name of business organization Buisness type
የሚይዘው የምርት ዓይነት ______________________________________________________________
Product Type
የድርጅቱ አድራሻ
Address of the organization
ክልል _____________________ዞን/ክ/ከተማ _________________ወረዳ ____________ከተማ _______________
Region Sub city/Zone Woreda City
ቀበሌ _______________ የቤ/ቁጥር___________ስ/ቁጥር ____________________ፋክስ________________
Kebele House no Telephone Fax

የድርጅቱ ባለቤት/ሀላፊ ሙሉ ስም ________________________________________
Owners Full Name

ድርጅቱ ባለስልጣኑ ያወጣውን መስፈርቶች ማሟላቱ ስለተረጋገጠ በምግብ፣ በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 661/2002 መሰረት ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡
This Certificate of Competence is issued upon fulfillment of requirements set by the Authority in accordance with Food, Medicine and Healthcare Administration and Control Proclamation No. 661/2009.

የሃላፊ ፊርማ _________________________ የተሰጠበት ቀን ____________________
Signature of Authorized Person Date of Issue

| | | |
|---|---|---|
| ታድሳል<br>Renewed<br>200____E.C/201___G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር _________<br>R/no<br>ፊርማ ____________<br>Signature | ታድሳል<br>Renewed<br>200____E.C/201___G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር _________<br>R/no<br>ፊርማ ____________<br>Signature | ታድሳል<br>Renewed<br>200____E.C/201___G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር _________<br>R/no<br>ፊርማ ____________<br>Signature |

ማሳሰቢያ /Notice/

ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት/ This certificate of competence/

1. በየአመቱ ካልታደሰ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡
   Shall be considered cancelled unless renewed every year.
2. ድርጅቱ አግባብ ካላቸው ህጎችና መስፈርቶች ውጭ ሲሰራ ሲገኝ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡
   May be suspended or revoked if the organization is found in violation of applicable laws & standards.

አዝል 5

## የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን
**Ethiopian Food, Medicine & Healthcare Adminstration & Control Authority**

## በመግቢያና መውጫ በር የምግብ ኢንስፔክሽን ቅፅ

1. የድርጅቱ ስም ________________________________የብ/ማ ምስክር ወረቀት ቁጥር _____
2. የመግቢያና መውጫ በር ________________________
3. የመ11ዣ ሰነድ ቁጥር ________________________
4. የኢንቮይስ ቁጥር ________________________
5. የዲክላራስዮን ቁጥር ________________________

| ተቁ | የምርቱ መግለጫ/ መጠሪያ ስም | መለኪያ | መጠን | የአምራቹ ድርጅት ስም | የምርት መለያ ቁጥር | የተመረተበት ቀን | የመጠቀሚያ ጊዜ ማብቅያ ቀን | መግለ ጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |

የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን
**Ethiopian Food, Medicine & Healthcare Adminstration & Control Authority**

## የምግብ ናሙና መውሰጃ ማሳወቂያ ቅጽ

እኔ/እኛ ስሜ/ስማችን ከታች የተገለፀው የባለስልጣኑ ኢንስፔክተር/ሮች የሆንኩኝ/የሆንን በምግብ፣ በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ (2) (መ) በተሰጠኝ/ን ስልጣን መሰረት የሚከተለውን የምግብ ናሙና ለምርመራ አላማ ከድርጅቱ የወሰድኩ/ን መሆኔን/ናችንን አረጋግጣለሁ/እናረጋግጣለን፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የናሙናው ባለቤት ድርጅት ስም | |
| 2 | የብቃት ማረጋገጫ ም/ወረቀት ቁጥር | |
| 3 | አድራሻ | |
| 4 | የናሙናው መጠሪያ ስም እና አይነት | |
| 5 | መጠን | |
| 6 | የምርት መለያ ቁጥር (batch No.) | |
| 7 | የተመረተበት ቀን | |
| 8 | የመጠቀሚያ ጊዜው የሚያበቃበት ቀን | |
| 9 | የአምራቹ ድርጅት ስም | |
| 10 | ናሙናው የተወሰደበት ቦታ | |
| 11 | ናሙናው የተወሰደበት ምክንያት | |

ናሙናውን የወሰደው ኢንስፔክተር ሙሉ ስም

1. ________________ፊርማ _____
2. ________________ፊርማ _____
3. ________________ፊርማ

የድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ

ስም ____________

ፊርማ ____________

ቀን __________ሰዓት ______

ናሙናው የተወሰደበት ቀን _______ሰዓት _____

የኢንስፔክተሮች ሀላፊ አስተያየት ________________________________________________

የሀላፊው ሙሉ ስም ______________________

ፊርማ ______________________

ቀን ______________________

እዝል 7

**የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን**
**Ethiopian Food, Medicine & Healthcare Adminstration & Control Authority**

# ናሙና ወደ ላቦራቶሪ መላኪያ ቅፅ

ለ ____________________________________________

በምግብ፣በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ (2) (P) መሰረት የሚከተለውን የምግብ ናሙና ለምርመራ አላማ የተላከ መሆኑን እየገለፅን ናሙናው ተመርምሮ የምርመራው ውጤት እንዲገለፅልን እንጠይቃለን፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የናሙናው መጠሪያ ስም እና አይነት | |
| 2 | መጠን | |
| 3 | የምርት መለያ ቁጥር (batch No.) | |
| 4 | ምግቡ የተመረተበት ቀን | |
| 5 | የመጠቀሚያ ጊዜው የሚያበቃበት ቀን | |
| 6 | የተመረተበት ሀገር | |
| 7 | የአምራቹ ድርጅት ስም | |
| 8 | ናሙናው ምርመራ ያስፈለገበት ምክንያት | |
| 9 | የምርመራ ዓይነት<br>(eg. microbiology, physicochemical, nutrional content, toxicicty etc….) | |

ናሙናው የላከው ሀላፊ

ሙሉ ስም ________________________

ፊርማ ________________________

ቀን ________________________

የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤናክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን
**Ethiopian Food, Medicine & Healthcare Adminstration and Control Authority**

## ምግብን ኳራንታይን የማድረጊያ መተማመኛ ቅፅ

እኔ/እኛ በስሜ/ስማችን ከታች የተገለፀው የባለስልጣኑ ኢንስፔክተር/ሮች የሆንኩኝ/የሆንን በምግብ፣ በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ (2)(P) በተሰጠኝ/ን ስልጣን መሰረት ዝርዝራቸው ቀጥሎ የተገለፀው ምግቦች ጥራታቸውና ደህንነታቸው እስኪረጋገጥ ድረስ በማንኛውም መንገድ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ኳራንታይን ተደርገው እንዲቆዩ ያዘዝኩኝ/ን መሆኔን/ናችንን አረጋግጣለሁ/እናረጋግጣለን፡፡

1. የምግቡ ባለቤት ድርጅት ስም ________________የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር ____________
አድራሻ ክልል _____________ዞን/ክፍለከተማ _______________ወረዳ __________ከተማ _______________
ቀበሌ ____________የቦታው ልዩ መጠሪያ ________________ስልክ ቁጥር __________
2. ምግቡ èራንታይን የተደረገበት አድራሻ ፤ ክልል _________ዞን/ክፍለከተማ ____________ወረዳ __________
ከተማ _____________ቀበሌ ___________የቦታው ልዩ መጠሪያ __________መጋዘን ቁጥር (ካለ) ___________

| ተ ቁ | የምግብ ዓይነት | የምርት መለያ ቁጥር | የተመረ ተበት ቀን | የመጠቀ ሚያው ማብቅያ ጊዜ | የአምራቹ ድርጅት ስም | የተመረተ በት ሀገር | መጠን | èራንታይን የተደረገበት ምክንያት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |

እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተገለፀው የዚህ ድርጅት ባለቤት/ተወካይ የሆንኩኝ የባለስልጣኑ ኢንሰፔክተሮች ባዘዙት መሰረት የያዝኩትን ምግብ ጥራትና ደህንነት እስኪረጋገጥ ድረስ በማንኛውም መንገድ ምግቡን ጥቅም ላይ እንዳይውል èራንታይን አድርጌ የማቆየው መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

የድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ ስም ________________________________

ፊርማ ______________________

ቀን _____________ሰዓት _____________

ኳራንታይን አድራጊው ኢንስፔክተር ሙሉ ስም

1. __________________________ፊርማ________
2. _______________________ፊርማ __________
3. _______________________ፊርማ __________

ኳራንታይን የተደረገበት ቀን _______ሰዓት _____

ማሳሰቢያ

ይህ ቅፅ በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ 1 ኮፒ ለድርጅቱ 1ኮፒ ከድርጅቱ ፋይል ጋር የሚያያዝ ሆኖ 1ኮፒ ለህግ ክፍል ለክትትል የሚላክ ይሆናል፡፡

## የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን
## Ethiopian Food, Medicine & Healthcare Adminstration and Control Aouthority

ቀን ____________ | የመልቀቂያ ፍቃድቁጥር ____

Date | Release permit no.

### በመግቢያና መውጫ በር የምግብ መልቀቂያ ማሳወቂያ ሰነድ
### Entry-Exit Port Food Release Notification

ለ ________________________________________________

To

ከዚህ በታች የተጠቀሰው ምግብ በምግብ፣ በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች መስፈርት የሚያማላ በመሆኑ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ/ ወደ ውጭ ሀገር እንዲወጣ ፈቃድ ተሰጥ~ል፡፡

The food item specified hereunder has been approved to be Imported/Exported to/from the country in accordance with the requirements of the Food, Medicine & Healthcare Adminstration & Control Proclamation No. 661/2009 and other relevant laws.

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የድርጅቱ ስም<br>Name of the Organization | |
| 2 | የመጓጓዣ ሰነድ ቁጥር<br>Bill of lading No. | |
| 3 | ኢንቮይስ<br>Invoice No. | |
| 4 | የዲክላራስዮን ቁጥር<br>Declaration number | |
| 5 | የምግቡ ዓይነት<br>Type of food | |
| 7 | ከኢንቮይሱ ውስጥ ወደ ሀገር እንዳይገባ/ከሀገር እንዳይወጣ የተከለከለ (ካለ)<br>Food not approved to be imported/exported from the invoice (if any) | |

| የምግብ ዓይነት (type of food) | መለኪያ (unit) | መጠን (Quantity) | የምርት መለያ ቁጥር (batch No) | ምግቡ የተመረተበት (Manf.date) | የአምራቹ ድርጅት ስም (Munufacturer) | የተመረተበት ሀገር (Country of origion) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

| | |
|---|---|
| የኢንሰፔክተር ሙሉ ስም ____________________<br>Name of aouthorised inspector<br>ፊርማ ________<br>Signiure<br>የተሰጠበት ቀን ________ አገልግሎት የሚያበቃበት ቀን ________<br>Date of issuance Valid up to | ማህተም<br>Seal |

ማሳሰቢያ፤

ይህ ፎርም በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ ዋናው ለጉምሩክ 2ኛው ኮፒ ለድርጅቱ የሚሰጥ ሆኖ 3ኛው ኮፒ ከፓዱ ጋር የሚቀመጥ ይሆናል፡፡

This form shall have three copies the orginal sent to custom & reveniue, the 2nd copy to the organization and the 3rd copy shall be kept along with the pad/

እዝል 10

**የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን**

**Ethiopian Food, Medicine & Healthcare Adminstration & Control Aouthority**


Telephone: +251115522547
Fax: +251115521392
P.o.box -5681
E-mail: regulatory@fmhaca.gov.et
Website-http://www.fmhaca.gov.et
Addiss Abeba- Ethiopia


Ref.No _______/_______/_______ Date: ________/______/_____

# HEALTH CERTIFICATE

This is to certify that ___________________________________ Ltd, Adress___________________________ Ethiopia is registered under certificate of competence No ___________in accordance with the Food, Medicine & Healthcare Administration & Control proclamation no. 661/2009 of Ethiopia, as a food _____. The food is inspected to ascertain compliance with the prescribed standard.

Permission is hereby granted to it for export of____________________________Metric Tons of__________________________________________________________________to _______as here under shown.

| | Name of food | Invoice Number | Batch no | Quantity (MT) | Values ($US) | remark |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | Total | | | | | |

Please note that this Health Certificate is limited to this consignment only, and is Valid from Date _________/_____/______to Date_____/____/_______.

Signed by:

___________________________________

Authorized person